# <u>እኛ ምን አገባን</u> !

(አለሙ አሎ)

እኛ ጥቅማችን ካልተነካ
አያገባንም ፖለቲካ።
ማንም ይፈታ አይፈታ
ለኛ አይሰጠንም አንዳች ደንታ።
ከሚዘርፈው ላይ ካካፈለን
ሰይጣን ቢገዛን ምን ቸገረን።
ከሚበሉት ውስጥ ከሚያስበሉ
የኛ ቤተሰብ ከሁሉ አሉ።
ፖለቲከኞች አትበጥብጡን
አርፈን እንብላ ሰላም ስጡን።
የተገረፈው የታሰረው
የኛ ልጅ አይደል የባዳ ነው።
ከኛ ቤተሰብ የታሰረ
እህት ወንድሙን የቀበረ
እናት አባቱን የገበረ
አንድም ሰው የለ የተነካ
አያገባንም ፖለቲካ።
የማሙሽ እናት ለሞተባት
የማሚቱ እናት ምን አገባት።
ተቀናቃኝን መግደል ማሰር
አዲስ አይደለም ለኛ ሐገር።
ሕይወት እንዲህ ነው ምን ይደረግ
ያንደኛው ለቅሶ ለሌላው ሰርግ።
አንደኛው ሞቶ ቦታ ሳይለቅ
ሌላው ወደ ላይ አይልም ፈቀቅ።
ይጩህ ይንጫጫ ያልቅስ ያንባ
ሲያሻው ሰፊው ህዝብ ገደል ይግባ።
እኛ አናስብም ከኛ ሌላ
ታሪክ ሰሪው ዝብ ታሪክ ይብላ።
ታሪክ ሰሪው ዝብ አስቸጋሪ
ቡትቶ ለባሽ ጦም አዳሪ
አለም ዘላለም ላያልፍለት
ስንቱ እንደበግ ታረደለት።
ያገባኛል ባይ ያገር ጉዳይ
ችግር ጋባዥ ነው በራሱ ላይ።
ትላንትም ዛሬ አላርፍ ያሉ
እናውቅ የለም ወይ የት እንዳሉ።
ሐገራችን ናት የምድር ገነት
አፍ ዘግቶ መብላት ላወቀበት።
የተገደለው የታሰረው
አፍ ዘግቶ መብላት የማይችል ነው።
ሰርተን አልሆነም አጭበርብረን
እናገኛለን ጤናው ካለን።
ባቋራጭ መክበር ከተቻለ
ካልፈጋሁ የሚል ማን ሞኝ አለ።
ከሁለት አንደኛው ይለይለት
አግኝቶ መኖር አለዚያም ሞት።
እፎይ ግልግል ከሞትንማ
ታሪክ ሲወቅሰን አንሰማ።
ትንሽ አሻሮ አንጠልጥሎ
ጠጋ ማለት ነው ወደ ቆሎ።
ማንም ምድራቱን ሲቀራመት

ድርሻዬን ባገኝ ምን አለበት።
አብሮ መንጠቅ ነው መመንተፍ
የናት ያባት ቤት ሲዘረፍ።
በዛሬ ጊዜ የቸገረው
ዘመኑን መምሰል ያቃተው ነው።
የዘመኑ ሰው የሚጮኸው
ልክ እንደ ውሻ ላበላው ነው።
ያንድነት መንፈስ ተሰበረ
ሐገሬ ማለት ድሮ ቀረ።
ክልላችን ነው የኛ ሐገር
የምን ኢትዮጵያ ብሎ ነገር።
ለኛ ካልኖረች ጥገት ሆና
ለምን አይወጣም ብትንትንዋ።
እኛ የምኖረው ለዛሬ ነው
የራሱ ጉዳይ የነገው ሰው።
ግደሉ ሲባል - በምኔ
ዝረፉ ሲባል ስንት ለኔ
ማለት የማይችል ገገማ ሰው
እኛ ክልል ውስጥ ቦታም የለው።
አህያም የለን እኛ ጎራ
ምን ያጣላናን ከጅብ ጋራ።
ትንሽ ጨጉዋራ ካካፈለን
ድሮም ለስጋ ደንታ የለን።
ስጋውን ይብላ ደም ይጠጣ
አጥንቱን ብቻ ለኛ ያምጣ።
ከኛ ቤተሰብ የታሰረ
እህት ወንድሙን የቀበረ
እናት አባቱን የገበረ
አንድም ሰው የለ የተነካ
አያገባንም ፖለቲካ።
አያገባንም ፖለቲካ።
አያገባንም ፖለቲካ።